# የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች የሥልጠና መርጃ ስብስብ

ሰዎችን መደበኛ የስልክ በይነመረብ
ክህሎቶችን ለማስተማር የተዘጋጀ መመሪያ



የቅጂ መብት © 2024 GSM Association

# ሞጁል 2፦ WhatsApp

## የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች የሥልጠና መርጃ ስብስብ

ሰዎችን መደበኛ የስልክ በይነመረብ ክህሎቶችን ለማስተማር የተዘጋጀ መመሪያ

## ይህ ምንድን ነው?

**በስልኩ ላይ WhatsAppን ያሳዩ።**

**ያብራሩ፡-** «WhatsApp የመልዕክት መላላኪያ አገልግሎት ሲሆን፣ በተወሰነ መልኩ ልክ እንደ አጭር የጽሁፍ መልዕክት መላኪያ አይነት እና የድምፅ መልዕክቶችን እና ፎቶዎች መላክን እንዲሁም ለብዙ ሰዎች መልዕክት መላክን ያካተተ ነው።»

«WhatsApp የበይነመረብ አየር ሰዓት ይጠቀማል፣ ስለዚህ መልዕክቶችን መላክ ርካሽ ሊሆን ይችላል እንዲሁም መልዕክት የሚልኩለት ሰው ያለበት ርቀት በዋጋው ላይ ለውጥ አያመጣም። ለምሳሌ፣ ወደ ሌላ አገር የሄደ የቤተሰብ አባል ወይም ጓደኛ ካለዎት፣ WhatsApp ላይ ለእሱ መልዕክት መላክ ይችላሉ እንዲሁም የሚልኩት መልዕክት ከቤትዎ ጎን ቢሆን እንዳለ ሲልኩ ከሚያስወጣዎት በላይ ወጪ አይጠይቅም።»

## የሚያስፈልጉዎ ቁሳቁሶች፡-



ስማርት ስልክ ቀፎዎች




የWhatsApp ፖስተሮች

## ለምን ሊጠቀሙበት ይችላሉ?

«ቪድዮዎችን በመስራት ወይም የድምፅ ጥሪዎችን በማድረግ ወይም መልዕክቶችን፣ የድምፅ ማስታወሻዎችን፣ ፎቶዎችን ወይም ቪድዮዎችን በመላክ ከቤተሰብዎ እና ከጓደኞችዎ ጋር በቀላሉ ግንኙነትዎን ለማስቀጠል ሊጠቀሙበት ይችላሉ።»

«እንዲሁም ትልቅ ቡድን ካካተተ የሥራ ባልደረቦች/ሰራተኞች/የክፍል ጓደኞች/ደንበኞች/የቁጠባ አጋሮች ጋር ለመገናኘት ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡- ምርቶችን ለማስተዋወቅ፣ ምክር ለማጋራት፣ የንግድ አጋርነቶችን እና ስምምነቶችን ለመፍጠር፣ ከክፍል የተሰጡ ማስታወሻዎች ወይም መልመጃዎች ላይ ለመወያየት።»

ስለ WhatsApp ጥቅሞች እና በግልዎ እንዴት እንደሚጠቀሙበት የራስዎን ምሳሌዎች ለሰልጣኞች ያጋሩ።

## ለምን ሊጠቀሙበት ይችላሉ?

**ለሰልጣኙ ሕይወት እንዴት** ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል በመወያየት ከሰልጣኙ ጋር የሚገናኝ እንዲሆን ያድርጉት። ለሚከተሉት የሰልጣኝ ዓይነቶች ተገቢ የሆኑ ምሳሌዎችን ታሳቢ ያድርጉ፡-

**አዛውንት፡-** መልዕክት በመለዋወጥ ወይም ማህበራዊ ሚዲያ በመጠቀም ከቤተሰብ ጋር እንደተገናኙ ይቆዩ፤ በመስመር ላይ ስለ ጤና መረጃ ይፈልጉ።

**እናት ወይም የቤት እመቤት፡-** የጤና ሠራተኞችን ያግኙ፤ ከጓደኞች እና ቤተሰብ ጋር ያለዎትን ግንኙነት ያስቀጥሉ፤ የእናቶች ቡድን ይቀላቀሉ።

**የንግድ ባለቤት፡-** ምክር ለማጋራት የሥራ ፈጠራ ቡድሮችን ይቀላቀሉ፤ ምርቶችዎን ወይም አገልግሎቶችዎን ያስተዋውቁ፤ ለደንበኛዎች ሽያጭ ይፈጽሙ፤ ስለ አዲስ ዕቃዎችዎ ለደንበኞች ያሳውቁ።

**ገበሬ ወይም የገጠር ሰው፡-** የገበሬ ቡድኖችን ይቀላቀሉ፤ ከገዢዎች እና ከሌሎች ገበሬዎች ጋር ይገናኙ፤ የሚሸጡ ምርቶችን ለገዢዎች ያሳውቁ።

**ወጣት፡-** ከጓደኞች ጋር ግንኙነትዎን ያስቀጥሉ፣ እንደ የትምህርት፣ የስፖርት ወይም የሥራ ቅጥር ዕድሎች የመሰሉ ቡድኖችን ይቀላቀሉ።

## እንዴት ነው የሚሰራው?

### ስልኩን በሰልጣኙ እጅ ላይ ያድርጉት እና ቅደም ተከተሎችን እንዲከተሉ ያግዟቸው።




**WhatsAppን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል – የአንድ ለአንድ መልዕክት መላላክ**

ፖስተሩን ያሳዩ እና ጽሑፍ፣ ፎቶ እና የድምጽ መልዕክት ለመላክ ቅደም ተከተሎችን ያከናውኑ።




**WhatsAppን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል – የቡድን መልዕክት መላላክ**

ፖስተሩን ያሳዩ እና የቡድን ውይይትን ለመጀመር ቅደም ተከተሎችን ያከናውኑ።

## ልምምድ ያድርጉ!

**«አሁን WhatsAppን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል አውቀዋል፣ ምን ለማድረግ ሊጠቀሙበት ይፈልጋሉ?»**

**አሰልጣኝ፡-** ሰልጣኙ በስልካቸው ላይ መልዕክት ሊልኩላቸው ለሚፈልጓቸው በስልክ ላይ ያሉ ሰዎች የWhatsApp መልዕክቶችን እንዲልኩ ድጋፍ ያድርጉ።

**ጠቃሚ ምክር፡-** «WhatsApp በርካታ ባህሪያት አሉት። ለምሳሌ፣ በWhatsApp ለሰዎች መደወል ወይም የት እንዳሉ እንዲያውቁ WhatsApp ላይ ላሉ ዕውቂያዎችዎ በካርታ ላይ መገኛ ቦታዎን ማጋራት ይችላሉ።»

ከWhatsApp ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ሌሎች የመልዕክት መላላኪያ አገልግሎቶች እንዳሉ **ያብራሩ**። ሌሎች ተመሳሳይ ምሳሌዎች፡- Messenger፣ WeChat፣ Telegram እና Viberን ያካትታሉ።

## ደህንነት

«WhatsApp ላይ ማንም ሰው ሊያገኝዎ እንደሚችል ያስታውሱ። ያን ሰው በደንብ የሚያውቁት ካልሆነ በስተቀር WhatsApp ላይ እንደ የተንቀሳቃሽ ስልክ ባንክ መረጃ፣ አድራሻዎ ወይም ሌላ የግል መረጃ ያሉ የግል ዝርዝሮችን በጭራሽ አያጋሩ።»



**«በመስመር ላይ ደህንነትዎን ለመጠበቅ ምርጥ ጠቃሚ ምክሮች» የሚለውን ፖስተር ያሳዩ።**

WhatsApp ሲጠቀሙ እነዚህ ጠቃሚ ምክሮች ምን ማለት እንደሆኑ ከሰልጣኞችዎ ጋር **ይወያዩ**።

ለሰልጣኝዎ ተገቢ የሆኑ ምሳሌዎችን በመጠቀም ጠቃሚ ምክሮቹ ህይወት እንዲኖራቸው ያድርጉ። ለምሳሌ፣ አንዳንድ ሰዎች WhatsAppን ስለሚጠቀሙ አጭበርባሪዎች ሊጨነቁ ይችላሉ፣ አንዳንድ ሴቶች ደግሞ ትንኮሳን እንዴት መከላከል እንደሚችሉ የበለጠ ሊያሳስባቸው ይችላል።

አጭር ሥልጠና፡-
WhatsApp

# ፖስተሮች እና ተቆርጠው የወጡ ማሳያዎች

## የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች የሥልጠና መርጃ ስብስብ

ሰዎችን መደበኛ የስልክ በይነመረብ ክህሎቶችን ለማስተማር የተዘጋጀ መመሪያ

GSMA

# በመስመር ላይ ደህንነትዎን ለመጠበቅ ምርጥ ጠቃሚ ምክሮች

**በይነመረብ በዓለም ዙሪያ ላሉ ሰዎች ሁሉ ክፍት መሆኑን ያስታውሱ፣ ስለዚህ እንደ እውነተኛው የህዝብ መገናኛ ቦታ (ለምሳሌ፣ የገበያ ቦታ) ማየቱ አስፈላጊ ነው እንዲሁም ራስዎን በመጠበቅ እና በመስመር ላይ ለሚያደርጉት ነገር ኃላፊነት በመውሰድ ደህንነትዎን ይጠብቁ።**

## በመስመር ላይ የሚመለከቱት ነገር ሁሉ እውነት እንዳልሆነ ያስታውሱ

ማንኛውም ሰው ማንኛውንም ነገር በመስመር ላይ መለጠፍ ይችላል፣ ስለዚህ የሚመለከቱትን ሁሉ አይመኑ። ከሚያምኑት ሰው እንኳን ቢሆን እውነት ላይሆን ይችላል። መረጃን ለሌሎች ከማጋራትዎ በፊት ጥንቃቄ ያድርጉ።

## በመስመር ላይ ለተዋወቁት ሰው ገንዘብ ከመላክዎ በፊት ደግመው ያስቡ

ያልጠየቋቸውን ኢሜይሎች፣ መልዕክቶች ወይም ብቅ-ባዮች በተለይም ገንዘብ የሚጠይቁ ከሆኑ ወይም እንግዳ የሆኑ አገናኞችን ከያዙ ይጠንቀቋቸው።

## የይለፍ ቃሎችን ጨምሮ የግል መረጃዎን ለግልዎ ያቆዩ

በጣም አስፈላጊ ካልሆነ በቀር፣ እንደ ሙሉ ስምዎ፣ የቤት አድራሻዎ ወይም ስልክ ቁጥርዎ ያሉ የግል ዝርዝሮች ማጋራት የለብዎትም።

## በመስመር ላይ በሚገኙ ሌሎች ሰዎች ላይ ጉዳት አያድርሱ

መልካምነትን እና አክብሮትን ያሳዩ። ጉልበተኝነት አያሳዩ፣ የውሸት መረጃን አያሰራጩ ወይም ማንም ሰው ላይ ትንኮሳ አያድርሱ። በመስመር ላይ የሚወስዷቸው እርምጃዎች በእውነተኛ ሕይወት ላይ ያሉ ሰዎች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ።

## ማጭበርበሮችን እና አጭበርባሪዎችን ይወቁ

ልክ በእውነተኛ ሕይወት እንዳለው ሁሉ፣ በበይነመረብ ላይም ሌቦች እና ወንጀለኞች አሉ። አንዳንድ ሰዎች በመስመር ላይ ሌላ ሰው እንደሆኑ ያስመስላሉ።

## የሚያስቸግርዎትን ሰው በማገድ ወይም ችላ በማለት እርምጃ ይውሰዱ

የሆነ ሰው በመስመር ላይ ካስቸገረዎ ወይም ትንኮሳ ካደረሰብዎ፣ እርዳታ ይጠይቁ እንዲሁም ለሆነ ሰው ይናገሩ ወይም ሪፖርት ያድርጉ።

# የዳታ ወጪዎች



WhatsApp
እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

# የአንድ-ለአንድ መልዕክት መላክ



WhatsApp
እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

# የቡድን መልዕክት መላክ

1




2




3



WhatsApp
እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

# እንዴት ማገድ እንደሚቻል

1




⋮

2




ተጨማሪ

3




አግድ

4




አግድ

ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች

**WhatsApp**

ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች

**WhatsApp**



ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች

**WhatsApp**



ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች

**WhatsApp**



ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች
WhatsApp



ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች
WhatsApp

